በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር
ለስምጥ ሸለቆ ኃይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን
ሀዋሳ

ጉዳዩ፡- የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 19 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 10 ገጽ አባሪ በድምሩ 29 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 30 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ
የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር

የስምጥ ሸለቆ ኃይቆች ተፋስስ ባለሥልጣን

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር

የስምጥ ሸለቆ ኃይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የስምጥ ሸለቆ ኃይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የሆስፒታሉ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡ -

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የስምጥ ሸለቆ ኃይቆች ተፋሰስ ባለስልጣን ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

<u>የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

የስምጥ ሸለቆ ኃይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን ሥራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 13 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAG.F-02.19/3/8 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መጋቢት 6 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር ስሸሐ/መ-012/861 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

1.1 <u>በደንብና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>፤

1.1.1 <u>ግኝት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በተለያዩ የተሰብሳቢ የሂሳብ ኮዶች (መደቦች)፡-

1. ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ ብር **1,871,575.22**፣
2. ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ ብር **346,847.16** ፣

በድምሩ ብር **2,218,422.38** በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ መሆኑ ታውቋል፡፡
(ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.1.2 <u>ሥጋት</u>

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ፡-

- ☞ ገንዘቡ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል፡፡
- ☞ ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም፡፡

1.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል።

1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ✓ በ4201 ብር 1,302.77 ከተለያዩ ሰራተኞች የሚሰበሰብ በመሆኑ በ2010 በጀት ዓመት ሰብስበን ገቢ እናደርጋለን።
- ✓ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4210 ብር 1,871,575.22 የሚታይ ሲሆን፣ ተሰብሳቢ ሂሳቡ በተፋሰሱ ስር ካሉ ወረዳዎች ያልቀረቡ ወይም በጥሬ ያልተመለሱ በመሆኑ የሚታይ ነው። በቀጣይ የክፍያ ሰነዶች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲወራረዱ የተቻለንን እናደርጋለን።
- ✓ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4211 ብር 345,544.39 ከግገር ሰራተኛ ሊሰበሰብ የሚገባ በመሆኑ ግለሰቡ ገንዘቡን ወደ መንግስት ካዝና እንዲመልሱ በተደጋጋሚ ቢገለጽም ምላሽ ባለመስጠታቸው ምክንያት ክስ ተመስርቶባቸው በክትትል ላይ እንገኛለን ።

1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

- ✓ በተፋሰስ ወረዳዎች ላይ ያለው ተሰብሳቢ ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲወራረድ መደረግ ይኖርበታል ።
- ✓ ከግገር ሰራተኛ ላይ የሚፈለገው የነዳጅ ግገር ተሰብሳቢ ሂሳብ በተያዘው የህግ አግባብ ተገቢው ክትትል በማድረግ የመንግስት ገንዘብ ሊሰበሰብ እንዲችል ጥረቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መደረግ እንዳለበት እናሳስባለን።

2. ተከፋይ ሂሳብ

2.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ፤

2.1.1 ግኝት

በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚገኙ ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ

ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በ5009 ሂሳብ ኮዶ (መደብ) ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቆየ ብር 1,459.95 የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።

2.1.2 <u>ሥጋት</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

2.1.3 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብና መመሪያ መሠረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ ተገቢው ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

2.1.4 <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5009 ብር 1,459.95 ለህክምና የተሰበሰበና ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ገቢ የሚደረግ ይሆናል።

2.1.5 <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

የተከፋይ ሂሳብ ወቅቱን ጠብቆ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ እናሳስባለን።

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

3.1 <u>አላግባብ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ስለመኖሩ</u>፤

3.1.1 <u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 በአንቀጽ 6(1) የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈጸመው ወይም ወጪ የሚደረገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ እንደሆነ በመመሪያው ላይ ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ:-

1. ለብሄረ አማራ ዴሞክራሲ ንቅናቄ (ብአዴን) 36ኛ ዓመት የምስርታ በዓል በሚል ብር 5,000.00፣

2. ለአርባ ምንጭ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በባንክ ቁጥር 1000021677047 ለእስፖንሰር ሺፕ ተብሎ ብር 20,000.00፣

በድምሩ ብር 25,000.00 ክፍያ በጀቱ ከተያዘለት ዓላማ ወጪ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል።

3.1.2 ስጋት

- ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- በበጀት ላልተያዘ ጉዳይ ክፍያ መፈጸም ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ይችላል።

3.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የመንግሥት በጀት የሚፈቀደው በእቅድ ለተያዙ ጉዳዮች ስለሆነ ለተጠቀሰው ጉዳይ የሚፈቀድ በጀት እንደሌለ እየታወቀ ክፍያ መፈጸሙ አግባብነት የሌለው ስለሆነ አሰራሩ ሊስተካከል ይገባል።

3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በትብብር ስለሚሰራ የባለስልጣን መሥሪያ ቤቱን ገጽታ የሚገነባ ሆኖ ያገኘነው ስለሆነ በተለይም መንግሥት ባወጣው የዩኒቨርስቲዎች ኢንዱስትሪ ትስስር መሰረት ከሐዋሳ፣ ከዲላ፣ ከአርባምንጭ፣ ከአርሲ፣ ወልቅጤ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የትብብር ስምምነት ስላለው ክፍያውን ልንፈጽም ችለናል።

3.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ለእስፖንሰር ሺፕ ተብሎ የሚያዝ በጀት በሌለበት ሁኔታ ክፍያ መፈጸም ተገቢ ባለመሆኑ አሰራሩ እንዲስተካከል መደረግ ይኖርበታል።

3.2 ተገቢው ማስረጃ ያልቀረበለት የወጪ ሂሳብ፤

3.2.1 ግኝት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ግምሩክ ባለስልጣን ነሀሴ 2001 ዓ.ም ባወጣው የደረሰኝ አያያዝ አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 28/2001 ክፍል 4

ተራ ቁጥር 3 ላይ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ ግብር/ታክስ ከፋይ የሚጠቀምበት ደረሰኝ፡-

1. ተከታታይነት ያለው የደረሰኝ ቁጥር ቀንና ዓመተ ምህረት፣
2. የድርጅቱን ስምና አድራሻ፣
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣
4. የአቅርቦቱን ዓይነት፣መጠን፣ ነጠላና ጠቅላላ ዋጋ እንዲሁም
5. የታክስ ምጣኔ እና የገንዘቡን መጠን፣

የሚሉትን መሠረታዊ መረጃዎች መያዝ እንዳለበት ይደነግጋል። ሆኖም መጋቢት 27 ቀን 2009 ዓ.ም በወጪ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 197081 በሂሳብ መደብ 6221 በሂሳብ ብር 11,104.00 ለነንሰቦ ወረዳ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ለተከናወነ 69.4 ኪሎ የቡና ዘር ግዢ ህጋዊ የሆነ ደረሰኝ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል።

3.2.2 ሥጋት

- የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ይችላል።
- ለገንዘብ ብክነትና ጥፋት መንገድ ሊከፍት ይችላል።
- አቅራቢው ታክስን ለመሰወር ሊጠቀምበት ይችላል።

3.2.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የደረሰኝ አያያዝ አጠቃቀምና ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር 28/2001 ክፍል 4 ተራ ቁጥር 3 ላይ በተመለከተው መሰረት መሥሪያ ቤቱ በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ካልተመዘገቡ ግብር/ታክስ ከፋይ አቅራቢዎች ግዥ ሲፈጸም መቀረብ ያለበት ደረሰኝ ከላይ በግኝቱ ላይ በዝርዝር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ያሟሉ መሆን እንዳለባቸው ለማሳሰብ እንወዳለን።

3.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ክፍያው የተፈፀመው በሻሸመኔ ወረዳ ሲሆን ፋክቱር በሌላቸው ፎርም ክፍያው ሲፈጸም ወረዳው የቡና ዘር ግዥ ለመፈጸም በዞኑ ውስጥ ነንስቦ ወረዳ ቡናና ሻይ ባለስልጣን መሥሪያ ቤት ብቻ ሲሆን ዞኑም በቃለ

ጉባኤና በደብዳቤ ገልጾልናል። ለወደፊት አስተያየቱን ተቀብለን በጥንቃቄ የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

3.3 ውል ላልገቡ ሰራተኞች የተፈጸመ ክፍያ፤

3.3.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ቁጥር 4 የመደበኛና የካፒታል ሥራ ማስኬጃ ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢው የወጪ ማስረጃ መቅረቡ መረጋገጥ እንዳለበት ተመልክቷል። በዚሁ መሰረት መሥሪያ ቤቱ ክፍያዎችን መፈጸሙን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በሀዋሳ ሀይድሮሎጂ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እና በማዕከላዊ የሀይድሮሎጂ ጣቢያዎች የሚሰሩ የሰራተኞች ዝርዝር የሰው ኃይል እና የክፍያ መጠንን አስመልክቶ ከኢፌድሪ የውሃ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ጋር ሐምሌ 11 ቀን 2008 ዓ.ም በቃለ ጉባኤ በቁጥር ውመአሚ66/10/281 ርክክብ ፈጽሟል። ነገር ግን ከሀምሌ ወር 2008 እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ለሰሩበት ክፍያ ሲፈጸም በየትኛው ጣቢያ እንደሚሰሩ ያልታወቁና ውል ላልተገባላቸው ሰዎች ብር 45,600.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል። (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

3.3.2 ሥጋት

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል።
- ☞ ሥራውን ላላከናወኑ ሰዎች ክፍያ ሊፈጸም ይችላል።

3.3.3 የማሻሻያ ሃሳብ

በርክክቡ ወቅት ያልተገለጹ በየትኛው ጣቢያ እንደሚሰሩ ያልታወቁና ውል ላልተገባላቸው ሰዎች የተፈጸመው ክፍያ አግባብነት ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል።

3.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በርክክቡ ወቅት በመስክ ከሁለቱም መሥሪያ ቤቶች በተወጣጡ ባለሙያዎች የመስክ ምልከታ ተደርጎ በአጠቃላይ 49 ጣቢዎች የተለዩ ሲሆን በእነዚህ ጣቢያዎች የሚሰሩ የቀን ሰራተኞች በ2009 በጀት ዓመት በተሰጠው አስተያየት መሠረት ውል በማስገባት በአሁኑ ሰዓት በማስራት ላይ እንገኛለን፡፡

3.4 ለውሎ አበል ክፍያው ተገቢ የሆነ ማስረጃ ሳይቀርብለት የተፈጸመ ክፍያ፤

3.4.1 ግኝት

በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተፈጸሙት የውሎ አበል ክፍያዎች ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ.ም የሲቪል ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በቁጥር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ30/ጠ13/40/883 በተላለፈው መመሪያ መሰረት ለመሆኑ በናሙና ኦዲት ሲደረግ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች ያልሆኑና ከየት መሥሪያ ቤት እንደመጡ፤ የደመወዛቸው መጠን፣ የሥራ ደረጃቸውና ለስራ የላካቸው መሥሪያ ቤት አበል እንዳልከፈላቸው የሚገልጽ የመገጣጠሚያ ደብዳቤ ሳይቀርብ ለአምሰት ግለሰቦች ብር 29,200.00 የውሎ አበል ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

(ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

3.4.2 ሥጋት

- ☞ የውሎ አበል ክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ አያስችልም፡፡
- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል፡፡

3.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ክፍያው የተፈጸመለቸው ግለሰቦች ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ መደረግ እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በውሎ አበል አከፋፈል ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

3.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

ስለሁኔታው በደብዳቤ ጠይቀን የመጡ የፓርላማ አባላት የህዝብ ተመራጭ ስለሆኑ ደብዳቤ ሣያቀርቡ ክፍያ የፈፀምን ሲሆን ለወደፊት በተሰጠን አስተያየት መሰረት የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

3.4.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የፓርላማ አባላትም ቢሆኑም የውሎ አበል ክፍያውን ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚሸፍን ለመሆኑ ተገቢው የጽሁፍ ማስረጃ ከመጡበት መሥሪያ ቤት ባልቀረበለት ሁኔታ የክፍያውን አግባብነት ማረጋገጥ አይቻልም። ስለሆነም የምክር ቤት አባላት በመሆናቸው ብቻ ክፍያ ሊፈጸም አይገባም። ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ የአሰራር ሥርዓቱን ተከትሎ የውሎ አበል ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል። ስለሆነም ከመጡበት መሥሪያ ቤት የውሎ አበል ክፍያ ያልተፈጸመ ለመሆኑ እና ክፍያው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በኩል መፈጸም ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ማረጋገጫ ደብዳቤ ሊቀርብ ይገባል።

3.5 በጨረታ መፈጸም ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ የመኪና አገልግሎት ግዥ፤

3.5.1 ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 መሠረት የመደበኛና የካፒታል ሥራ ማስኬጃ ክፍያ ለሚፈጸምባቸው ወጪዎች ተገቢ የሆነ የወጪ ማስረጃ መቅረቡን መረጋገጥ እንዳለበት ያመለክታል። በዚሁ መሰረት፡-

1. ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለመኪና ኪራይ የፈጸመውን ክፍያ ብር 353,871.25 ትክክለኝነትን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣
   - ✓ ግዥው በጨረታ ተፈጽሞ ተገቢው ውል መፈጸም ሲገባው ግዥው በዋጋ ማወዳደሪያ እንዲፈጸም የተደረገ መሆኑ፤

- ✓ የመኪና ኪራይ አገልግሎቱ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት አገልግሎቱን የጠየቀው ክፍል ለመጠቀሙ እንዲያረጋግጥ እና ከየሥራ ክፍሉ የሚቀርበው የግዥ መጠየቂያ ከአገልግሎት ክፍያ ጥያቄው ጋር እንዲያያዝና እንዲመሳከር ያልተደረገ መሆኑ፤
- ✓ በተሰበሰበው የዋጋ ማወዳደሪያና በግዥ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ ሰነድ የአገልግሎት ግገርው ያስፈለገው ከመቼ እስከመቼ ለመጠቀም እንደሆነ አለመገለጹ፤

2. የባለሥልጣኑ ሰራተኞች ለመስክ ስራ ለተሰማሩባቸው መኪኖች ለቀዱት ነዳጅ ያቀረቡት ደረሰኝ በመስክ ስራ በተሰማሩባቸው አካባቢ እና በስራ ላይ በነበሩባቸው ቀናቶች መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለነዳጅ ተብሎ የተፈጸመው ክፍያ ብር 6,466.12 ለመስክ ሥራ ከተሠማሩባቸው ሥፍራ ውጪ መሆናቸው፤

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 4 እና 5 ተያይዟል)

3.5.2 ሥጋት

1. ለመኪና ኪራይ የአገልግሎት መጠየቂያ የማይቀርብ ከሆነ የአገልግሎት ግዥው የሚፈለግበት ቀናት ካልታወቀና ተገቢው የውል ሥምምነት ካልተፈጸመ፡-
   - ☞ የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል ።
   - ☞ በሥራ ሂደት ወቅት ሊከሰቱ የሚችሉ ሁኔታዎችን ለመፍታት አስቸጋሪ ሁኔታ ለፈጠር ይችላል።

2. በውሎ አበል ክፍያና የነዳጅ ግዥ የተፈጸመበት ቦታ ከተለያየ፡-
   - ☞ የክፍያውን አግባብነት ለማረጋገጥ አይቻልም።
   - ☞ የውሎ አበል ክፍያው ወይም የነዳጅ ግዥው ተገቢነት ላይኖራቸው ይችላል።
   - ☞ የክትትልና የቁጥጥር ሥራው ላይ ክፍተት መኖሩን ሊያመለክት ይችላል።

3.5.3 የማሻሻያ ሃሳብ

- ✓ ግዥ ከመፈጸሙ በፊት የአገልግሎት ግዥ መጠየቂያ ሊቀርብ ይገባል፡፡
- ✓ የአገልግሎት ግዥው ሊከናወን የሚገባው የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ በተገቢው የግዥ ዘዴ ሊሆን ይገባል፡፡
- ✓ ለአገልግሎት ግዥው ተገቢው ውል ሊፈጸም ይገባል፡፡
- ✓ በውሎ አበል ክፍያና የነዳጅ ግዥ የተፈጸመበት ቦታ መለያየት አለአግባብ የተፈጸመ ክፍያ መኖሩን የሚያመለክት በመሆኑ ሁኔታው ተጣርቶ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡

3.5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የመኪና ኪራይ ክፍያ የተፈጸመው ሶስት የተለያዩ የመኪና አከራይ ድርጅቶች ከአሸነፉ በኋላ የተሟላ አገልግሎት ባለመስጠታቸው ከተለያዩ ድርጅቶች በማወዳደራችን እንጅ ከአንድ ድርጅት ብቻ 353,897.25 አልተቃወምንም ቢሆንም የቀሩት አስተያየቶች ተቀብለን የምንስተካክል መሆኑን እንገልጻለን፡፡

3.5.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የመኪና ከራይ ግዥ የግዥ መመሪያውን ተከትሎ በተገቢው የግዥ ዘዴ እንዲፈጸም እንዲሁም ለነዳጅ ተብሎ የተፈጸመው ክፍያ ብር 6,466.12 ሁኔታው ተጣርቶና ለውሎ አበል ከተፈጸመው ክፍያ ጋር ተገናዝቦ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያም ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም ነዳጅ ተገዝቶ በሚቀርቡ ፋክቱሮች እና በውሎ አበል አከፋፈል ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

3.6 ከመመሪያ ውጪ የተፈጸመ የዉሎ አበል ክፍያ፤

3.6.1 ግኝት

ሰኔ 2004 በወጣው የመንግሥት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ አንቀጽ 3 መሰረት አንድ የመንግሥት ሠራተኛ ከመደበኛ

የሥራ ቦታው ውጪ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሂዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራትና ለአልጋ በሰራተኛው የደመወዝ መጠን ልክ የውሎ አበል ተመን ክፍያ እንደሚፈጸም ያመለክታል:: ይሁን እንጂ:-

1. የመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ሲሄዱ ሠራተኞች ለተጓጓዙበት መኪና ከተፈጸመው የኪራይ ክፍያ ሰነድ ለመረዳት እንደተቻለው ሰራተኞቹ መኪናውን የተጠቀሙት ከሰኔ 5 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 11 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ለ7 ቀናት ያህል መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። ሆኖም ሰራተኞቹ ለጉዞ ለቆዩባቸው ቀናቶች ተብሎ የ20 ቀን የውሎ አበል የተፈጸመ ከመሆኑም በተጨማሪ ክፍያው ሰራተኞቹ በጉዞ ወቅት ለቁርስ፣ ለምሳና ለእራት በተጠቀሙበት እንዲሁም ለአልጋ ባደሩበት ቦታ በመመሪያው መሰረት የውሎ አበል ክፍያው መፈጸም ሲገባው ሙሉ ክፍያው ባልተጓጓዙበት መስመር በባህር ዳር ከተማ ተሰልቶ በመከፈሉ ምክንያት አላግባብ ብር **110,580.00** ተከፍሎ መገኘቱ፤
2. የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ላልሆኑ በአባሪው በተራ ቁጥር 30 እና 31 ለተመለከቱት አቶ ኃይሉ አርቃ እና አቶ እሸቱ ቦልካ ለተባሉ ግለሰቦች በጠቅላላው ብር 6,242.00 የውሎ አበል ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

3.6.2 ሥጋት

የውሎ አበል መመሪያውን ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም:-

- ☞ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ይችላል::
- ☞ ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሣጣው ይችላል።
- ☞ በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ያለውን ክፍተት ሊያመለክት ይችላል።

3.6.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ከመመሪያው ወጪ የተፈጸመው የውሎ አበል ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ የመሥሪያ ቤቱ ባልደረባ ሳይሆኑ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም የውሎ አበል ክፍያ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም አጥብቀን እናሳስባለን። ከመመሪያ ውጭ ክፍያውን የፈቀዱት ኃላፊዎችም ሊጠየቁበት ይገባል።

3.6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተሰጠን አስተያየት መሰረት እናስተካክላለን።

3.6.5 የኦዲተሩ አስተያየት

አለአግባብ የተፈጸመው ክፍያ በሙሉ ተመላሽ እንዲሆን፤ ለወደፊቱም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የውሎ አበል ክፍያ የወጣውን መመሪያ ተከትሎ እንዲፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

3.7 ያልተቀነሰ የሥራ ግብር እና የወጪ መጋራት ታክስ ስለመኖሩ፤

3.7.1 ግኝት

1. በገቢ አዋጅ ቁጥር 979/2008 ክፍል 2 አንቀጽ 10 የደመወዝ ገቢ ግብር የሚቀነስ መሆኑን፣
2. ስለከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2008 አንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው መሰረት ተጠቃሚው ከምረቃ በኋላ ሥራ ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወር ውስጥ ወይም ከምረቃ በኋላ ከአንድ ዓመት በኋላ የሚፈለግበትን ክፍያ ተቀጣሪ ከሆነ ከወር ገቢው በየወሩ ቢያንስ አሥር በመቶ (10%) ከገቢ ተከፋይ በሆነ መልክ እየቀነሰ ወይም በሙያው በግሉ የተሰማራ ከሆነ ከዓመት ገቢው በዓመቱ የሚፈለግበትን መጠን ተሰልቶ መክፈል ያለበት መሆኑን፣

ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ✓ በነባር ደመወዝ ላይና በጭማሪው ደመወዝ መካከል ሊሰበሰብ የሚገባና ያልተሰበሰበ የስራ ግብር ብር 551.35 መኖሩ፤
- ✓ ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በአዲሱ ደመወዝ መሰረት ብር 5,291.00 ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራት መኖሩ፤

ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 7 እና 8 ተያይዟል)

3.7.2 ሥጋት

- ☞ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም ያሳጣዋል።
- ☞ መንግሥት ያወጣውን አዋጅ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

3.7.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ተቀናሽ ያልተደረገው የሥራ ግብር እና የወጪ መጋራት ክፍያ በመመሪያው መሰረት ተሰብስቦ ለገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ገቢ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም የደመወዝ ክፍያ ሰነድ ሲዘጋጅ ተቀናናሽ ሂሳቦች በትክክል ለመሰላታቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል።

3.7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተሰጠን አስተያየት መሰረት አስተካክለናል።

3.7.5 የኦዲተሩ አስተያየት

በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ ለመሆኑ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል።

4. ንብረት

4.1. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ ክፍተቶችን በተመለከተ፤

4.1.1 ግኝት

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ዕቃዎችን ለመየለየት በማያስችል ሁኔታ ተደባልቀው የተቀመጡ መሆኑ፤
2. አሮጌና የማያገለግሉ የመኪና ተመላሽ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞ/19 ያልተዘጋጅላቸው መሆኑ፤
3. ዋጋቸው በብር 45,043.48 የሚያወጡ አራት ጠረጴዛዎች ከሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ ሳይውሉ ተደራርበው በግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
4. በተጠቃሚ እጅ ላይ የሚገኝ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በተጠቃሚዎቹ ያልተፈረመ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.1.2 ሥጋት

- ☞ ንብረቶች ለብልሽት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡
- ☞ በንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

4.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈፀም መደረግ ይኖርበታል፡፡

4.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተሰጠን አስተያየት መሰረት አስተካክለናል፡፡

4.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

በተሰጠው የማሻሻያ አስተያየት መሰረት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ ለመሆኑ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡

5. በጀት

5.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

5.1.1 ግኝት

ለባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል ወጪ በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶቹ ሲታይ ከ10% በላይ፡-

- ከመደበኛ በጀት ብር 2,096,417.41፣
- ከካፒታል በጀት ብር 4,518,583.48፣

በድምሩ ብር 6,615,000.89 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል፡፡

(ለዝርዝሩ አባሪ 9 ተያይዟል)

5.1.2 ሥጋት

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በእቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የባለስልጣኑን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

5.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ሐገሪቷ ያላትን ውስን በጀት በማብቃቃት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ በተለይም በጎላ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሳይውሉ በቀሩት የሂሳብ ኮዶች ላይ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

በተሰጠን አስተያየት መሠረት እንሰራለን፡፡

5.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

ኤጀንሲዉ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

6. ልዩ ልዩ

6.1 የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፈው በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች፤

6.1.1 ግኝት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሠረት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጪ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄድ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ ተገልጾ በተሰጠው አስተያየት መሰረትም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

6.1.2 ሥጋት

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፡-

- ☞ ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ይችላል።
- ☞ ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

6.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሥጋት ምንጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የሥጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ማድረግ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን።

6.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

የሥጋት ምጮች ዳሰሳ፣ የተጋላጭነት ደረጃ መለየት እና የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ መደረግ እንዳለበት ያመንን ሲሆን፣ በቀጣይ በተሰጠን አስተያየት መሰረት የምንሰራ መሆኑን እንገልጻለን።

6.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት

የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ የሚደረገው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም በሚያደርገው እንቅስቃሴ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሥጋቶችን በመለየትና ምንጫቸውን በማወቅ፣ የሥጋት ደረጃና (Level of Risk) የተጋላጭነት አቅም (Probability of Occurrence) ተገንዝቦ ይህንን ሥጋት ለመቀነስ ከተቻለም ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት ነው። ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ በመመሪያው መሠረት ተቋማዊ የሥጋት ተጋላጭነት ግምገማ ቢያደርግ ጠቃሚነቱ የጎላ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን!!!

አባሪ.1

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ የቆይታ ጊዜን የሚያሳይ ዝርዝር</u>፤

ተራ ቁጥር	የሂሳብ መደብ ቁጥር	የተሰብሳቢ ሂሳቡ ክፍያ የቆይታ ጊዜ	የቆይታው ጊዜ			ድምር
			ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆየ	ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የቆየ	ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አስር ዓመት ድረስ የቆየ	
1	4201	ከ2003 እስከ 2009 በጀት ድረስ		**1,302.77**		**1,302.77**
2	4210	ከ2008 እስከ 2009 በጀት ድረስ	**1,871,575.22**			**1,871,575.22**
3	4211	ከ2003 እስከ 2009 በጀት ድረስ		**345,544.39**		**345,544.39**
		ድምር	**1,871,575.22**	**346,847.16**	**0.00**	**2,218,422.38**

አባሪ. 2

<u>በርክክብ ውስጥ ለሌሉ፣ ውል ላልተገባለቸወና በየትኛው ጣቢያ</u>

<u>እንደሚሰሩ ላልታወቁ ሰዎች የተፈጸመ ክፍያ ዝርዝር፤</u>

ቀን	የወጪ ቫውቸር ቁጥር	ክፍያው የተፈጸመው ሰው ሥም	ክፍያው የተፈጸመው ጊዜ	የቀን ብዛት	የቀን ክፍያ መጠን	ጠቅላላ ክፍያ
08/05/09	550850	ዳባዱ ኪሞ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		አየለ ገልዳዳ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ባይከዳኝ ጌታ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ዳዊት ዲንጋሞ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ብርሀኑ ሮዴቶ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ገቢ ደቀቦ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		አስናቁ አርጋው	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ተመስገን ታምራት	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ታደሰ ጉተማ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
30/06/09	551066	አስናቀ አርጋው	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ፍልገባ መሀመድ	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ገቢ ደቀሶ	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		አማን ገመዳ	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ኡርጌ ሳአሰና	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ፍልገባ መሀመድ	ከሀምሌ 1 እስከ ጥቅምት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ዳዊት ዲንጋሞ	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		አየለ ገልዳዳ	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		መኮንን ጎዳና	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
		ዳባ ዱክሞ	ህዳር1/2009 የካቲት 2009 ድረስ	120	20	2400.00
	ድምር					**45,600.00**

አባሪ. 3

<u>ለውሎ አበል ክፍያው ተገቢ የሆነ ማስረጃ ሳይቀርብለት የተፈጸመ ክፍያ ዝርዝር፤</u>

ቀን	ክፍያ የተፈጸመላቸው ሰዎች ዝርዝር	የወጪ ማስመስከሪያ	የተከፈላቸው ቀን ብዛት ከ-እስከ	የቀን የውሎ አበል መጠን	ጠቅላላ ተከፋይ
25/8/09	**አቶ ዳኘው በለጠ**	551303	20-29/08/2009	590.00	5,900.00
25/8/09	**ወ/ሮ አየኋት አሰፋ**	551304	20-29/08/2009	590.00	5,900.00
25/8/09	**አቶ ሞገስ ታደሰ**	551302	20-29/08/2009	590.00	5,900.00
6/10/09	**አቶ ውብነት በላይ**	0813502	06-15/10/2009	575.00	5,750.00
6/10/09	**አቶ ታምሩ ታፈ**	0813503	06-15/10/2009	575.00	5,750.00
ድምር					29,200.00

አባሪ. 4

<u>የውል ስምምነት፣ የአገልግሎት መጠየቂያ ያልቀረበበት እና ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ የመኪና ኪራይ ግዥና ክፍያን የሚሳይ ዝርዝር፤</u>

ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	የመኪና አከራይ ድርጅት	የገንዘብ መጠን
24/02/09	619211	**ማርሸት እሸቱ**	35,707.50
08/03/09	240345	**ጤናዬ የመኪና አከራይ**	34,787.50
12/04/09	619267	**ጤናዬ የመኪና አከራይ**	15,812.50
24/05/09	619286	**ጤናዬ የመኪና አከራይ**	75,900.00
08/06/09	619298	**ጤናዬ የመኪና አከራይ**	41,112.50
22/06/09	619339	**ጤናዬ የመኪና አከራይ**	26,881.25
28/10/09	619410	**ኤስ ኢ.ቲ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል**	101,320.00
28/09/09	619396	**ኤስ ኢ.ቲ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል**	22,350.00
ድምር			**353,871.25**

<u>በመስክ ሥራ ላይ ለመሆናቸው በውሎ አበል ከተገለጸው ከተማ ወጪ የተፈጸመ የነዳጅ ግዥ ዝርዝር፤</u>

ወጪው የተመዘገበበት ቀን	የቫውቸር ቁጥር	የሠራተኛው ሥም	ለሥራ የሄዱበት ሥፍራ	ውሎ አበል የተከፈለበት ቀን ከ እስከ	ነዳጅ የተሞላበት ቦታ	ነዳጅ የተሞላበት ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	የገንዘብ መጠን
25/12/08	85808	ደሳለኝ አንግሶ	ሰገን ህዝቦች(ኮንሶ)	ከ15/11/08-5/12/08	ሀዋሳ ነዳጅ ማደያ	18/11/08	115708	2191.00
30/03/09	196682	ኤሊያስ ደጊሶ	አርባምንጭ	ከ14/3/09-29/3/09	ሀዋሳ ነዳጅ ማደያ	17/03/09	155474	1,340.00
					ይርጋለም መንገድ ነዳጅ ማደያ	16/03/09	0320	950.00
30/04/09	196828	ግርማ ስዩም	ቡታጂራና ስልጤ ወረዳ	ከ10/4/09-30/4/09	ሀዋሳ ነዳጅ ማደያ	11/04/09	355081	913.92
30/08/09	87596	ብርሀኑ ለገሰ	አርባ ምንጭ	ከ19/7/09-04/8/09	አዋሳ ታፍ ነዳጅ	20/07/09	0065434	1071.20
ድምር								**6,466.12**

<u>ከመመሪያ ውጭ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ ዝርዝር ፤</u>

ተራ ቁጥር	ሥም	ደመወዝ	በባህር ዳር ተመን መሰረት የተከፈለ የቀን ዉሎ አበል	የቆይታ ጊዜ የተከፈለ	ለቆየበት ቀን ተብሎ የተከፈለ	በአሶሳ ተመን መሰረት መከፈል የነበረበት የቀን ዉሎ አበል	የቆይታ ግዜ	መከፈል የነበረበት	በብልጫ የተከፈለ
1	ቾምቤ አለሙ	2872	176	20	3520	144	7	1,008.00	2,512.00
2	አይናለም አቡኔ	2872	176	20	3520	144	7	1,008.00	2,512.00
3	ፍሬህይወት ዘለቀ	2514	176	20	3520	144	7	1,008.00	2,512.00
4	አብርሀም ገዕናሞ	1743	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
5	ተሰማ አራርሶ	1370	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
6	ጌታቸው ሀ/ማሪያም	1243	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
7	እስከዳር ዳንኤል	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
8	ሹሚቱ ዳኜ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
9	ነፃነት ተገኝ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
10	በረከት ዳንኤል	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
11	ሽብሬ ምትኩ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
12	ፌቨን ካቻራ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
13	አምባቸው አለማየሁ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
14	ሀይሉ አላሞ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
15	ታደሰ ኤርሚያስ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
16	አስቴር ሞጋ	1068	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
17	መሰረት ሮባ	1068	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
18	ምስክር ማሞ	1068	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
19	ገነት ካስትሮ	1068	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
20	ሰለሞን በልሁ	4867	134	20	4360	177	7	1,239.00	3,120.00
21	ሀይማኖት ሸጋው	3152	134	20	3520	144	7	1,008.00	2,512.00
22	ጃለኔ ጃሞቦ	1743	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
23	አማን በሪሶ	1743	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
24	መሀመድ አህመድ	1743	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
25	ጉተማ ደቀቦ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
26	ገዳ ሹቢሳ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
27	ገመዳ ቡንትራ	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
	የሚዞር ድምር				**77,400.00**			**22,365.00**	**55,035.00**
	የዞረ ድምር				**77,400.00**			**22,365.00**	**55,035.00**

ተራ ቁጥር	ሥም	ደመወዝ	በባህር ዳር ተመን መሰረት የተከፈለ የቀን ዉሎ አበል	የቆይታ ጊዜ የተከፈለ	ለቆየበት ቀን ተብሎ የተከፈለ	በአሶሳ ተመን መሰረት መከፈል የነበረበት የቀን ዉሎ አበል	የቆይታ ግዜ	መከፈል የነበረበት	በብልጫ የተከፈለ
28	**ንግስት ዳንኤል**	1068	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
29	**ኀሳዬ ፍቃዱ**	1182	134	20	2680	111	7	777.00	1,903.00
30	**ሀይሉ አርቃ**	6303	218	20	4360				
31	**እሼቱ ቦልካ**	6809	218	20	4360				
32	**ኢያሱ ዳንኤል**	7647	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
33	**ተስፋዬ ታደሰ**	6361	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
34	**ሸጌ ቀልቤሳ**	6036	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
35	**ገነት ስዩም**	6036	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
36	**ማቲዎስ ላቃሞ**	6036	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
37	**ትዕግስት ደሳለኝ**	5304	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
38	**ታደለች በላይ**	5304	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
39	**አማኑኤል ኤጂሶ**	5294	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
40	**ብርሀኑ ለገሰ**	4867	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
41	**ሮዛ ፈለቀ**	4269	218	20	4360	177	7	1,239.00	3,121.00
42	**ብርሀኑ ማኬቦ**	3810	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
43	**ወርቃፈራው ገለቱ**	3740	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
44	**ህይወት ገበየው**	3740	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
45	**ማቴዎስ መርሻ**	3740	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
46	**ፋናዬ ወርቁ**	3278	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
47	**መስከረም ወ/ዮሐንስ**	3278	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
48	**አጀቡሽ ገብሬ**	3278	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
49	**አስናማማው አያሌው**	2872	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
50	**ይበልጣል በላያ**	3152	218	20	3520	177	7	1,239.00	2,281.00
ድምር					**166,760.00**			**47,460.00**	**110,580.00**

አባሪ .7

ያልተቀነሰ የሥራ ግብር ዝርዝር ፤

ተራ ቁጥር	ቀን		የሥራ ኃላፊነት	ገንዘቡ የተከፈለው ሠራተኛ	አዲሱ ደመወዝ	ነባር ደመወዝ	የደመወዝ ጭማሪ	መቀነስ የነበረበት የሥራ ግብር	የተቀነሰ ሥራ ግብር	ያልተቀነሰ ሥራ ግብር
1.	30/06/09	197056	ዋና ሥራ አስኪያጅ	ዶ/ር ከበደ ካንቹላ	14,170.20	10,735.00	3,435.20	1,202.35	677.32	525.00
2.	30/06/09	197056	ሾፌር	አቶ በላይ ባንድራ	1,743.00	1,123.00	620.00	93.00	66.65	26.35
	ድምር									531.35

አባሪ. 8

ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በተከፈለው አዲስ ደመወዝ መሰረት ያልተሰበሰበ የወጪ መጋራትን የሚያሳይ ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	ሰም	የደመወዝ መጠን	የተቀነሰ የወጪ መጋራት	መቀነስ የነበረበት የወጪ መጋራት	ያልተቀነሰው ልዩነት	ያልተቀነሰው የወሩ ብዛት	በጠቅላላ ያልተቀነሰ
1.	ሱራፌል ዳዊት	7,443.00	571.80	744.30	172.50	5	862.50
2.	አበበ አሰሌ	6,361.00	484.50	636.10	151.60	5	758.00
3.	ግረማ ስዩም	6,361.00	484.50	636.10	151.60	5	758.00
4.	አሰለፈች ጌታቸው	6,361.00	484.50	636.10	151.60	5	758.00
5.	ብርሃኔ ይግረማ	4,576.00	335.90	457.60	121.70	5	608.50
6.	ፀጋዬ በለጠ	4,313.00	315.20	431.30	116.10	5	580.50
7.	ተጎመጀች ዳንኤል	3,810.00	277.40	381.00	103.60	5	518.00
8.	ተሻገር ታምራት	3,152.00	225.70	315.20	89.50	5	447.50
	ድምር	42,377.00	3,179.50	4,237.70	1,058.20	5	5,291.00

አባሪ. 9

ከ10% በላይ ያልተሰራበት የመደበኛና የካፒታል በጀት፤

የወጪ ሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	
			የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)
I. የመደበኛ በጀት				
የበጀት ኮድ 223 -01-01				
6211	200,000.00	171,836.80	28,163.20	14
6213	300,000.00	245,214.95	54,785.05	18
6218	100,000.00	82,560.50	17,439.50	17
6219	71,756.05	15,197.34	56,558.71	79
6243	215,000.00	164,596.50	50,403.50	23
6244	100,000.00	61,068.47	38,931.53	39
6251	15,000.00	5,000.36	9,999.64	67
6313	200,000.00	68,519.50	131,480.50	66
6231	1,000,000.00	876,807.06	123,192.94	12
6254	100,000.00	62,852.19	37,147.81	37
6255	100,000.00	58,409.96	41,590.04	42
6256	50,000.00	13,678.54	36,321.46	73
6257	15,000.00	8,245.35	6,754.65	45
6258	200,000.00	175,649.50	24,350.50	12
6259	20,000.00	3,284.39	16,715.61	84
የበጀት ኮድ 226-02-01				
6217	160,000.00	49,869.18	110,130.82	69
6218	5,000.00		5,000.00	100
6223	340,000.00	186,698.11	153,301.89	45
6251	90,000.00	67,695.00	22,305.00	25
6231	300,000.00	246,832.00	53,168.00	18
የበጀት ኮድ 226-02-02				
6217	175,000.00	126,797.10	48,202.90	28
6223	200,000.00		200,000.00	100
6231	500,000.00	267,393.00	232,607.00	47
6233	55,000.00	45,100.11	9,899.89	18
የበጀት ኮድ 226-02-03				
6213	70,000.00	120.00	69,880.00	100
6217	230,000.00	47,711.45	182,288.55	79
6218	5,000.00		5,000.00	100
6243	100,000.00	5,519.63	94,480.37	94
6231	240,000.00	201,494.00	38,506.00	16
6233	5,000.00	3,300.00	1,700.00	34

የወጪ ሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	
			የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)
የበጀት ኮድ 226-02-04				
6212	80,000.00	66,998.43	13,001.57	16
6213	50,000.00	1,449.00	48,551.00	97
6217	200,000.00	76,209.28	123,790.72	62
6233	24,400.00	13,630.94	10,769.06	44
ድምር	5,516,156.05	3,419,738.64	2,096,417.41	
II. የካፒታል በጀት				
የበጀት ኮድ 226-02-04-01-01				
6213	15,000.00		15,000.00	100
6217	200,000.00	89,386.19	110,613.81	55
6219	400,000.00	343,948.52	256,019.39	14
6221	500,000.00	429,517.21	70,482.79	14
6223	100,000.00		100,000.00	100
6251	150,000.00	97,635.00	52,365.00	35
6313	190,000.00	167,412.90	22,587.10	12
6231	300,000.00	229,064.00	70,936.00	24
6232	15,000.00	687.00	14,313.00	95
6255	500,000.00	385,490.04	114,509.96	23
6324	1,120,000.00	847,021.89	272,978.11	24
የበጀት ኮድ 226-02-04-01-02				
6114	500,000.00	432,602.00	67,398.00	13
6213	30,000.00		30,000.00	100
6217	130,000.00	79,853.57	50,146.43	39
6219	400,000.00	259,698.42	140,301.58	35
6221	500,000.00	427,089.18	72,910.82	15
6223	100,000.00		100,000.00	100
6251	100,000.00		100,000.00	100
6313	100,000.00	80,780.74	19,219.26	19
6231	200,000.00	159,018.00	40,982.00	20
6255	500,000.00	375,611.25	124,388.75	25
6324	900,000.00	694,176.05	205,823.95	23
የበጀት ኮድ 226-02-04-01-03				
6212	70,000.00	60,724.21	9,275.79	13
6213	20,000.00		20,000.00	100
6217	150,000.00	73,532.38	76,467.62	51
6219	970,000.00	837,493.62	132,506.38	14
6221	1,900,000.00	1,646,773.65	253,226.35	13
6223	400,000.00		400,000.00	100

የወጪ ሂሳብ መደብ	የተስተካከለ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	
			የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)
6251	200,000.00		200,000.00	100
6231	312,784.00	126,617.00	186,167.00	60
6232	90,000.00	32,970.00	57,030.00	63
6255	480,000.00	305,652.75	174,347.25	36
የበጀት ኮድ 226-02-04-01-04				
6217	50,000.00	4,834.95	45,165.05	90
6223	600,000.00	-	600,000.00	100
6251	479,200.00	-	479,200.00	100
6231	50,000.00	15,810.00	34,190.00	68
ድምር	12,721,984.00	8,203,400.52	4,518,583.48	
ጠቅላላ ድምር	18,238,140.05	11,623,139.16	6,615,000.89	

<u>በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር</u>

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ___________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ___________________________

የተዘጋጀበት ቀን፡ - ___________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን፡፡